MAJANG FOREST BIOSPHERE RESERVE

የመጀንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ

የተፈጥሮና ባህል ትስስር ውበት መገለጫ







MELCA-Ethiopia

EMBASSY OF SWEDEN

የመጀንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ መልካ ኢትዮጵያ

በጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የሚገኘው የመጀንግ ደን ደኑን በዘላቂነት ለመጠበቅ የሚረዱ ድንቅ ብዝሀ ህይወት፣ ባህላዊ ዕሴቶችና አሰራሮችን የታደለ ደን ነው። የመጀንግ ደን በሀገራችን ኢትዮጵያ ከቀሩት ጥቂት እርጥበታማ የተፈጥሮ ደኖች አንዱና ዋነኛው ነው። ከዚህም በተጨማሪ ደኑ በሀገሪቱም ሆነ በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ሰፊና ወጥ የሆነ ደን እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ።



የመጀንግ ደን በሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በባዮስፌር ሪዘርቭነት ተመዝግቦ ከዓለም የባዮስፌር ሪዘርቮች መረብ እንዲቀላቀል ተደርጓል። በዚህም መሰረት የመጀንግ ደን በባዮስፌር ሪዘርቭነት ሐምሌ ወር 2009 ዓ.ም ላይ ተመዝግቧል። በዓለም ዙሪያ በ131 ሀገራት ከሚገኙ 727 ባዮስፌር ሪዘርቮች የመጀንግ ደን በባዮስፌር ሪዘርቭ 669ኛው ባዮስፌር ሪዘርቭ ሆኖ ተመዝግቧል።

የመጀንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ ጠቅላላ ስፋት 224,924 ሄክታር ሲሆን ይህም በሶስት ዞኖች የተከፋፈለ ነው። የባዮስፌር ሪዘርቩ ሶስት ዞኖችም ጥብቅ/ማዕከላዊ ዞን፣ አዋሳኝ ዞን እና የመተላለፊያ ዞን በመባል ይታወቃሉ።

ጥብቅ/ማዕከላዊ ዞን፥ ከባዮስፌሩ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት አኳያ በቂ ስፋት ያለውና ለጥብቅነት የተከለለ የደኑ ክፍል ነው። ማዕከላዊ ዞኑ በዘላቂነት እንዲጠበቅ በሚመለከተው አካል የህግ ማዕቀፍ የሚዘጋጅለት ሲሆን ዞኑ በተለይ በውስጡ የሚገኘውን ብዝሀ ህይወት በዘላቂነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የታለመ ነው። በዚህም መሰረት በጥብቅ ደኑ ውስጥ ከምርምርና የክትትል ስራዎች ውጭ ያሉ በደኑ ላይ ጫና የሚያሳድሩ እንቅስቃሴዎች በህግ የተከለከሉ ናቸው።





አዋሳኝ ዞን፥ ይህ ዞን በጥብቅ/ማዕከላዊ ዞኑና በመተላለፊያው ዞን መካከል የሚከለል ሲሆን ዓላማውም በዋነኛነት ማዕከላዊ ዞኑን ከሰዎችና እንስሳት ንክኪ መጠበቅና እንዲሁም በደኑ ላይ የጎላ ተጽዕኖ የማያሳድሩ የልማት ስራዎች የሚካሄዱበት ዞን ነው። በዚህም መሰረት በዚህ ዞን ውስጥ አነስተኛ የደን ውስጥ ግብርና፣ የአካባቢ ጥበቃ ትምህርት፣ የተለያዩ የደን ምርምሮች፣ ደኑ በሳሳባቸው አካባቢዎች ተጨማሪ የዛፍ ችግኝ ተከላ ሊካሄድ ይችላል።





የሽግግር ዞን፥ የህ ዞን የመኖሪያ አካባቢዎችን ጨምሮ በዘላቂ ልማት መርሆዎች ላይ የተመሰረቱ ልማቶችና ሌሎች የመሰረተ ልማት ስራዎች የሚካሄዱበት ዞን ነው።



ብዝሀ ህይወትና ባህል

- 550 የሚደርሱ የዛፍ ዝርያዎች, 33 አይነት አጥቢ የዱር እንስሳት, 180 የወፍ አይነቶች, እና 20 የተሳቢ እንስሳትዝርያዎች እንደሚገኙ በጥናት ተረጋግጧል

- በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ: ቢያንስ 27 ዕጽዋት 5 የወፍ አይነቶች እና 3 ተሳቢ እንስሳት

- 5 ወፎችን፣ 3 አጥቢዎችን፣ 3 ተሳቢዎችንና 28 የዕጽዋት አይነቶችን ጨምሮ የ 39 ሊጠፉ የተቃረቡ (IUCN ባለ ቀይ ምልክት ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ) የእንስሳትና ዕጽዋት አይነቶች መገኛ

- ጥልቅ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ባህል

ዘላቂ ልማትን መደገፍ

- የጫካ ማር፣ ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ እንሰት እና የተለያዩ ፍራፍሬዎች የመሳሰሉ ለአካባቢው ማህበረሰብ የኑሮ መሰረት የሆኑ ምርቶች መገኛ

- ዘላቂና በደኑ ላይ ተጽዕኖ የማያደርስ የግብርና ኢንቬስትመንት

- ኢኮ ቱሪዝም


- በሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊነት ያላቸው ኦርጋኒክ የግብርና ምርቶች











የማንበር አገልግሎት

-የመጀንግ ደን በናይል ተፋሰስ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ያላቸው ዋና ዋና ተፋሰሶች ጥበቃ፣ እንዲሁም በብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ጎርፍና የአፈር መሸርሸርን በመከላከልና ከፍተኛ መጠን ያለው ካርበን ከአየር ላይ በመምጠጥ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ከመከላከል አኳያ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

- የመጀንግ ደን እንደ አልዌሮ፣ ጊሎና አኮቦ የመሳሰሉ የነጭ አባይ ዋና ዋና ገባር የሆኑ ወንዞች መነሻ ነው።

- የ 550 ዕጽዋት ዝርያዎች፣ 33 አጥቢ እንስሳት፣180 የወፍ ዝርያዎችና 20 አጥቢ እንስሳት መገኛ ነው።

የሎጂስቲክስ ድጋፍ አገልግሎት

-ከአካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥበቃና ማንበር ስራዎችና ዘላቂ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶችን፣ የአካባቢ ጥበቃ ትምህርትና ስልጠናዎችን፣ እንዲሁም ጥናትና ምርምሮችንና የክትትል ስራዎችን የመደገፍ አገልግሎት።









የመጀንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ ልዩ ገጽታዎች

በማንኛውም ወቅት አረንጓዴነቱ የማይቀየር እርጥበታማ የተፈጥሮ ደን

የመጀንግ ደን በሀገራችን ከቀሩት ጥቂት እርጥበታማ (afromontane) እና በተለያይነት ከበለጸጉ የተፈጥሮ ደኖች አንዱ ነው።

ጥልቅ የሆነ ተፈጥሮን የመንከባከብና የመጠበቅ ባህል


በመጀንግ የሚገኙ ነባር ብሄረሰቦች ከትውልድ ትውልድ ሲወራረስ የቆየና ጥልቅ የሆነ ደንን የመንከባከብና የተፈጥሮ ሀብትን በዘላቂነት የመጠቀም ባህል ያላቸው ናቸው።


ክልላዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸው ተፋሰሶች አካል

የመጀንግ ደን በናይል ተፋሰስ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ ያላቸው ዋና ዋና ተፋሰሶች አካል በመሆኑ ለነዚህ ተፋሰሶችና በውስጣቸው ለሚገኙ ብዝሀ ህይወት ጥበቃና ጎርፍና የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ቁልፍ ሚና የሚጫወት ነው።

የተለያዩ የግብርና ምርቶች መገኛ

በማጃንግ የሚመረቱ የግብርና ሰብሎች፣ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች እንዲሁም ከተፈጥሮ ደኑ የሚሰበሰቡ እንደ ማር፣ ቡናና ቅመማ ቅመም የመሳሰሉ ምርቶችና የተፈጥሮ ደኑ ራሱ ከማህበረሰቡ ባህል ጋር የሚፈጥሩት ህብረት ውበት ከመሆኑም በላይ ሰዎች ከተፈጥሮ ጋር ተስማምተው የሚኖሩበት አካባቢ ማሳያ የሚሆን ምሳሌ ነው።





ስለ መጀንግ ደን ባዮስፌር ሪዘርቭ በጥቂቱ

መገኛ ስፍራ: መጀንግ ዞን፣ ጋምቤላ ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ከፍታ: 1500-2500 ከባ.ጠ.በ
ጠቅላላ የቆዳ ስፋት: 224,924 ሄክታር
ማዕከላዊ ዞን: 43882 ሄክታር
የመሸጋገሪያ ዞን: 73397 ሄክታር
የመተላለፊያ ዞን: 107645 ሄክታር
የህዝብ ብዛት: 60,000
የዞን ከተማ: ሜጢ



United Nations
Educational, Scientific and
Cultural Organization

Man and
the Biosphere
Programme

MAN AND THE BIOSPHERE PROGRAMME

By decision of the
International Co-ordinating Council
of the Programme on Man and the Biosphere,

Majang Forest
Ethiopia

has been designated for inclusion
in the World Network of Biosphere Reserves.

The world's major ecosystem types and landscapes
are represented in this Network, which is devoted to conserving
biological diversity, promoting research and monitoring,
as well as seeking to provide models of sustainable
development in the service of humankind.

Participation in the World Network faciliates cooperation
and exchanges at the regional and international levels.

DATE OF INSCRIPTION
14 June 2017

DIRECTOR-GENERAL OF UNESCO

የመልካ ኢትዮጵያ አድራሻ

ስ.ቁ: +251115507172
ፋክስ: +251115544556
ፖ.ሳ.ቁ: 1519 ኮድ 1250
www.melcaethiopia.org
facebook.com/melcaethiopia
Youtube/MELCA Ethiopia
twitter.com/EthiopiaMelca
t.me/melcaethiopia
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ